# የኢሳፕ ዜና መጽሔት

ቅፅ 1 | መስከረም 2006

## ውድ አንባቢ፣

የማኀበራዊ አገልግሎቶች ከለላ መርኃግብር (Protection of Basic Services - ፒቢኤስ) አካል የሆነው ሁለተኛው የኢትዮጵያ ማኀበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር (Ethiopia Social Accountability Program -ኢሳፕ) በክልል፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ በመንግሥት በመተግበር ላይ ይገኛል። የዓለም ባንክ በሚያስተዳድረው የበርካታ ለጋሾች የአደራ ፈንድ የሚረዳው የኢትዮጵያ ማኀበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር የመንግሥት ተወካዮች፣ የሲቪል ማኀበራትና የልማት አጋሮችን በሚያካትት ጥምር ኮሚቴ የሚመራና ክትትል የሚደረግበት ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ የኢትዮጵያ ማኀበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር በብቃት መተግበሩን ለማረጋገጥ የሥራ አመራር ኤጀንሲ ተቋቁሟል። የኢሳፕ2 አጠቃላይ ግብ ለኢትዮጵያውያን ዜጎች የሚቀርቡ መሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ጥራት ለማሳደግ የዜጎች ማኀበራትና መንግሥት አብረው ለመሥራት የሚችሉበትን አቅም ማጠናከር ነው።

እንደ ሥራ አመራር ኤጀንሲ፣ ስለመርሃግብሩ የእናንተን የመረጃ ፍላጎቶች ለማሟላት በመሻት የመጀመሪያውን የኢሳፕ2 የዜና መጽሔት በማተማችን በጣም ደስተኞች ነን። ባለፉት ሳምንታትና ወራት በሥራ አመራር ኤጀንሲው በኩል ምን እየተከናወነ እንደሆነና እስከዛሬስ ምን ውጤቶች ተመዝግበዋል የሚሉ ማብራሪያና ትክክለኛ መረጃ የሚሹ እጅግ በርካታ ጥያቄዎችን ተቀብለናል። ከዚህ ዕትም ጀምሮ በየሦስት ወሩ እንዲወጣ የታሰበው ይህ የዜና መጽሔት ከጥያቄዎቻችሁ ውስጥ የተወሰኑትን እንደሚመልስ እና በኢትዮጵያ የማኀበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር የአፈጻጸም የሚገኝበትን ደረጃ በተመለከተ ጠቃሚ የዳራ መረጃ እንደሚሰጣችሁ ተስፋ እናደርጋለን። ይበልጥ ጥልቅ የሆኑ መረጃዎችን እና ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን ታገኙ ዘንድ የፌስቡክ ገጻችንን እና ድረገጻችንን እንድትጎበኙም እንጋብዛችኋለን።

አስተያየታችሁን እንጠብቃለን።

ለሁላችሁም መልካም ንባብ እና 2006 የደስታ ዓመት እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።

ሮልፍ ሑኒንክ፣ የኢሳፕ2 የቡድን መሪ

## ኢሳፕ2 በካርታ ላይ

ኢሳፕ2 በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ ከ50 በላይ የሲቪል ማኀበራት ድርጅቶችን እየደገፈ የሚገኝ ሲኾን፣ እነዚህ የሲቪል ማኀበራት እና ድርጅቶች ፕሮጀክቶችን የሚተገብሩባቸው አካባቢዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት እና የተሰማሩባቸው መስኮችን የተመለከቱ መረጃዎችን በግልጽ ለማየት እንዲቻል፣ መስተጋብራዊ ካርታ ሠርተን በድረገጻችን ላይ አስቀምጠናል።

ካርታው ኢሳፕ2 የሚተገበርባቸውን ክልሎችን፤መስኮችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ሲኾን፣ በኢትዮጵያ የተለያዩ ወረዳዎች የማኀበራዊ ተጠያቂነት እንቅስቃሴዎችን በመተግበር ላይ ለሚገኙት የሲቪል ማኀበራት እና ድርጅቶች ምጥን መረጃዎችን ያቀርባል። በአሁኑ ወቅት፣ ይበልጥ በወረዳዎቹ ላይ ትኩረት ያደረገና ስለ ሲቪል ማኀበራት ድርጅቶቹም፣ የፕሮጀክት ቦታዎችን ባካተተ መልኩ የበለጠ መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችል ሰፋ ያለ መረጃ የሚሰጥ አዲስ ካርታ እያዘጋጀን እንገኛለን።

የኢሳፕ2 ድረገፅን መጎብኘትዎን ይቀጥሉ፣ አዲሱን ካርታ ያገኙ ዘንድም ከድረገጻችን አይራቁ!




## የድጋፍ መርኃግብር

የኢሳፕ2 መርኃግብር በኢትዮጵያ የማኀበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክቶችን ለሚተገብሩ የሲቪል ማኀበራት እና ድርጅቶች ገንዘብ ድጋፍ ያስገኛል። በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ክልሎች በተመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በትምህርት፣ በጤና፣ በውሃ አቅርቦትና ንጽህና፣ በግብርና እንዲሁም በገጠር መንገዶች ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ የህዝብ አገልግሎቶች አቅርቦትና ጥራት ዙርያ የዜጎች ፍላጎቶችና ችግሮችን ለሚቀርፉ የማኀበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል ከ10 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገንዘብ ተመድቧል።




Ethiopia Social Accountability Program Phase 2

## የገንዘብ ድጋፍን የተመለከተ መረጃ

እስከዛሬ ድረስ ኢሳፕ2 በ142 ወረዳዎች ለሚከናወኑ የመጀመርያ እና የሁለተኛ ሩብ ዓመት የማኅበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር እቅድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል ከ 2 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ለሰላሳ (30) የማኅበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር ፈጻሚ አጋሮች አከፋፍሏል። የመጀመርያው የገንዘብ ድጋፍ የማኅበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር ፈጻሚ አጋሮቻችን ቢሮዎቻቸውን እንዲያደራጁ፣ ሠራተኞችን እንዲቀጥሩና፤ ደሞዝ እንዲከፍሉ፣ እንዲሁም የፕሮጀክት ይፋ ማድረጊያ ክንዋኔዎችን እንዲያዘጋጁ አስችሏቸዋል። የሥራ አመራር ኤጀንሲው ከሁሉም የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች ከመጀመርያዎቹ ሁለት የሩብ ዓመት የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርቶች ጋር ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ ጥያቄዎችን ተቀብሏል። በቀጣዮቹ ሳምንታት የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች የመነሻ ጥናቶች እንዲያካሂዱ፣ የግንዛቤ ወርክሾፖች እንዲያዘጋጁና የማኅበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎች ላይ ሥልጠናዎችን ለዜጎች፣ ለአገልግሎት ሰጪዎች እና ለመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሰጡ በማገዝ ፕሮጀክቶቹን ፈር የሚያስይዝ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። ስለዚህም፣ በእነዚህ ተግባራት አፈጻጸም ዙርያ ወቅታዊ መረጃዎች ይዞ ብቅ የሚለውን ቀጣይ እትማችንን ይጠብቁ።

## የድጋፍ ስምምነት ወቅታዊ መረጃ

የሥራ አመራር ኤጀንሲው ከተጨማሪ 19 የማኅበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች ጋር ስምምነቱን ያገባደደ ሲኾን፣ በአሁኑ ወቅት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶቹ በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የተሻሻሉ ምክረሐሳቦቻቸውን እና በጀት እየላኩ ይገኛሉ። የሥራ አመራር ኤጀንሲው በስምምነት ሂደት ላይ የተሰጡ አስተያየቶች በተገቢው መልኩ መካተታቸውን ለማረጋገጥ ምክረሐሳቦቹን መከለስ የጀመረ ሲኾን፣ ይህንን ተከትሎም በአጭር ጊዜ ውስጥ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ይፈረማል። በመቀጠልም ለፈጻሚ አጋር ድርጅቶች የፕሮጀክት ባለሙያዎችፕሮጀክቶቻቸውን በተገቢው መንገድ በመስክ ላይ እንዲተገብሩት በጥሩ ሁኔታ ለማዘጋጀት የታለመ የቅድመድጋፍ ሥልጠና ይሰጣል።

# ዜና

## የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክለሳ የማኅበራዊ ተጠያቂነት ጥምር ኮሚቴ የፕሮጀክት ጉብኝት አካሄደ

የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የለጋሽ አገራትና የዓለም ባንክ ተወካዮችን ያካተተ የጥምር ኮሚቴ አባላት ያሉበት ቡድን በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም በአማራ ክልል በፎገራ፣ ደብረታቦር እና ማቻከል ወረዳዎች፣ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በጉባ ወረዳ የመስክ ጉብኝቶች አካሂዷል። የአስተባባሪ ኮሚቴው ቡድን አረጋውያን፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ከኤች.አይ.ቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ጨምሮ ከማኅበረሰብ አባላት ጋር ተገናኝተዋል። በተጨማሪም፣ የአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ አገልግሎት ሰጭዎችና የማኅበረሰብ አባላት ከተካተቱበት የማኅበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎች ተወካዮች ጋር ውይይት አድርገዋል። ቡድኑ የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ያሳዩት እመርታ አድናቆት አሳድሮባቸዋል። በቡድኑ የተጎበኙት የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች መርኃግብሩን በይፋ መጀመር፡ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን የሰጡና የወረዳ ማኅበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎችን ማቋቋምና የአገልግሎት አሰጣጡን መገምገም ጀምረዋል። የመርኃግብሩ ተሳታፊዎች ግልጽነት የሚታየባቸው ሲኾን፣ በመርኃግብሩ ትግበራ፣ በችግር አፈታት ሂደትና በአካባቢያቸው ልማት ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አገልግሎት ሰጭዎች የማኅበረሰብ ችግሮችን የመስማት ፍላጎት ያላቸው ሲኾን፣ ለፍላጎቶቹም በቂ ምላሽ መስጠት የሚቻልበትን መንገድ ለመፈለግ ዝግጁነት አሳይተዋል። መርኃግብሩ ለማኅበረሰቡ በሚሰጡት አገልግሎቶች ላይ ማኅበረሰቡ የባለቤትነት ስሜት እንዲያጎለብት ማድረጉን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ለምሳሌ በፎገራ ወረዳ ዜጎች የመድኃኒት እጥረት መኖሩን፣ የግንባታ ቁሳቁሶች አለመኖርንና የጤና ባለሙያዎች በተለይ በምሽት የማዋለድ አገልግሎት አለመስጠታቸው መፍትኄ የሚሹ ችግሮች መሆናቸውን ለይተው ጠቅሰዋል። ‹‹መንግሥት ሁሉንም ችግሮቻችንን ሊያስወግድልን እንደማይችል እንገነዘባለን፤ ነገር ግን አንዳንድ ችግሮቻችንን ለመፍታት እኛም ጉልበታችንን፣ ጊዜያችንን እና ገንዘብም ጭምር ለማዋጣት ፈቃደኞች ነን›› ሲሉ ተናግረዋል። ቡድኑ ለውይይት አመቻቾች ተጨማሪ ሥልጠና የመስጠትን፣ እንዲሁም በማኅበራዊ ተጠያቂነት ጽንሰሐሳብና ስልቶች ዙርያ የበለጠ ግንዛቤ ለማስረጽ ፈጻሚ አጋሮች መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ የማድረግን አስፈላጊነት ተገቢ ትኩረት እንደሚሻ አስታውቋል። ኮሚቴው አባላት በቀጣዮቹ ወራትም ተመሳሳይ ጉብኝቶችን በሌሎች መርኃግብሩ በሚፈፀምባቸው ወረዳዎች ያካሂዳሉ።





## ኢሳፕ2 አዎንታዊ አስተያየቶች ተቀበለ

ኢሳፕ2፣ ግንቦት 1 ቀን 2005 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የዓለም ባንክና ለጋሾች አባል በሆኑበት የግምገማ እና የአተገባበር ድጋፍ የጋራ ስብሰባ ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን አቀረበ:: ውይይቱ የተመራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር ዴ.ኤ.ታ የተከበሩ ዶ/ር አብረሃም ተከስተ የክልል፡ የወረዳ የመንግስት ሃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት ለኢሳፕ2 የበለጠ ቁርጠኝነት እና የባለቤትነት ስሜት እንዲዳብር ጥሪ አድርገዋል:: ዶ/ር አብረሃም ኢሳፕ2 የመንግሥት መርኃግብር መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል:: ምንም እንኳ መርኃግብሩ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ 142 ወረዳዎች እየተተገበረ ቢሆንም፣ የመጨረሻ ግቡ ማኅበራዊ ተጠያቂነት በጎ ተሞክሮዎች በአገሪቱ በሚገኙት 900 ወረዳዎች እውን እንዲሆን በማድረግ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ያለመ መሆኑን አስረድተዋል::

## የየኢሳፕ2 ጥምር ኮሚቴው እስከ 2007/08 ዓ.ም በጀት አፀደቀ

ጥምር ኮሚቴ በግንቦት ወር 2005 ዓ.ም ፣ አጠቃላይ የኢሳፕ2 በጀትን ከ14 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወደ 21,088,000 (ሃያ አንድ ሚሊዮን ሰማንያ ስምንት ሺህ) የአሜሪካ ዶላር በማሳደግ አፀደቀ:: በቪ.ኤን.ጂ ዋና መሥሪያ ቤት የፕሮጀክት ዳይሬክተር የሆኑት ሚስተር ሮልፍ ስዎርት በጀቱ በፀደቀበት ስብሰባ ላይ የተሳተፉ ሲኾን፣ የኢሳፕ2 ፕሮጀክት በጀት ማሳደጊያ በመጽደቁና ፕሮጀክቱ እስከ 2007/08 ዓ.ም እንዲቀጥል በመደረጉ መደሰታቸውን ተናግረዋል:: ተጨማሪ ገንዘብ መገኘቱ የሥራ አመራር ኤጀንሲው በኢትዮጵያ ለሚንቀሳቀሱ ለተጨማሪ 19 የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች የፕሮጀክት ድጋፍ ለማድረግ ያስችለዋል:: ሚ/ር ስዎርት በተለይ ከአስተባባሪ ኮሚቴው ለተሰጠው ገንቢ አስተያየትና መመሪያ አድናቆታቸውን የገለፁ ሲኾን፣ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ደኤታ ዶ/ር አብረሃም ተከስተ እንደተጠቀሰው ማኅበራዊ ተጠያቂነትን ለስኬት የማብቃትን አስፈላጊነት አስምረውበታል::

## ኢሳፕ2 አጠቃላይ የማጠናከሪያ ሥልጠና አካሄደ

ኢሳፕ2 ግንቦት 13 እና 14፣ 2005 ዓ.ም በማኅበራዊ ተጠያቂነት፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በቁጥጥር እና ምዘና፣ እንዲሁም በኮሚውኒኬሽን ላይ ያተኮረና የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች የፕሮጀክት ባለሙያዎች የተሳተፉበት አጠቃላይ የማጠናከሪያ ሥልጠና አካሄደ:: በጥር እና የካቲት ወር 2005 ዓ.ም የተካሄደው የቅድመድጋፍ ሥልጠና ቀጣይ የሆነውና ለግማሽ ቀን የተካሄደው የማጠናከሪያ ሥልጠና የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች ወደ ትግበራ ምዕራፍ በሚገቡበት ጊዜ በማኅበራዊ ተጠያቂነት አተገባበር ዙርያ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል ያለመ ነው:: ተሳታፊዎችም ሥልጠናው የአተገባበር ስልቱን የበለጠ ግልጽ እንዳደረገላቸው ተናግረዋል:: ሥልጠናው ከ30 ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች የተውጣጡ 90 ተሳታፊዎች የታደሙበት ሲኾን፣ በኢሳፕ2 መርኃግብር ተጠቃሚ ከሆኑ የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች የመጀመርያዎቹ ናቸው::



## የማኅበራዊ ተጠያቂነት ስልቶች

‹‹ልጆቼ ጥራት ያለው ትምህርት እያገኙ ስለመሆናቸው ማወቅ እፈልጋለሁ።›› ይህ በአካባቢያቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽነት እና ጥራት አስመልክቶ ዜጎች ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። የማኅበራዊ ተጠያቂነት ስልቶች በመጀመርያ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብና እነዚህን መረጃዎች በመጠቀም የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ለሚያገለግሉት ህዝብ የገቡትን ቃልኪዳን በመፈፀም ዙርያ ተጠያቂ ለማድረግ እና እኒህን መሰል የዜጎች ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችላሉ።

በኢሳፕ2፣ ስድስት የማኅበራዊ ተጠያቂነት ስልቶች ሥራ ላይ የዋሉ ሲኾን፣ በእነርሱም ዙርያ ሥልጠናዎች ተሰጥተው በወረዳ ደረጃ በማኅበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች አማካይነት በትክክል ተግባራዊ መደረጋቸው በሥራ አመራር ኤጀንሲው ክትትል ይደረጋል። እነዚህም ስልቶች፡ የማኅበረሰብ ደረጃ መስጫ ካርድ፣ የዜጎች አስተያየት መስጫ፣ የማኅበረሰብ ካርታ ሥራ፣ አሳታፊ የዕቅድ አወጣጥና በጀት አመዳደብ፣ ሥርዓተጾታን ታሳቢ ያደረገ በጀት አመዳደብ፣ ማኅበራዊ የኦዲት ሥራ እና የመንግሥት ገንዘብ አወጣጥ ክትትል ናቸው።

ከእነዚህ ስልቶች አንዱ የሆነው የማኅበረሰብ ደረጃ መስጫ ካርድ፣ ዜጎች ተጠቃሚ የሆኑበትን አንድ የህዝብ አገልግሎት በግል ስሜታቸው ላይ በመመሥረት የሚመዝኑበት ሲኾን፣ በአገልግሎቱ ያገኙትን የእርካታ መጠን ለመግለጽ፣ ጥሩ ሥራ ሲሰራ ለማበረታታት፣ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ቅሬታ የቀረበባቸው ጉዳዮች መፍትኄ ካላገኙ መወሰድ አለባቸው ብለው የሚያስቡትን ተጨማሪ እርምጃ ለመጠቆም የሚያስችል ነው። ዜጎች ለምሳሌ በአካባቢያቸው በሚገኝ የጤና ማዕከል አንዲት ነርስን ስለ ጤና ሁኔታቸው ምክር፣ አልያም ስለሚያስፈልጋቸው ህክምና መረጃ ጠይቀው ነርሷ ተገቢ ያልሆነ መስተንግዶ ብታሳያችው እና ለጤና ማዕከሉ ኃላፊ በግንባር ለመናገር ቢፈሩ ዜጎች ይህን መሣርያ መጠቀም ይችላሉ። በልጁ ላይ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣ መምህርን ለማመስገንና ለማበረታታት የሚፈልግ፣ ነገር ግን በምን መልኩ ይህንን ማድረግ እንደሚችል የማያውቅ አንድ ዜጋ (ወላጅ) የማኅበረሰብ ደረጃ መስጫ ካርድን መጠቀም ይችላል። ይህ መሣርያ በእጃቸው ካለ፣ ዜጎች ማኅበረሰብአቀፍ የህዝብ አገልግሎቶችን ጥራት፣ ተደራሽነት፣ ብቃት እና ውጤታማነት ለመቆጣጠር ይችላሉ። እንደማንኛውም የማኅበረሰብ ተጠያቂነት መሣርያ፣ የማኅበረሰብ ደረጃ መስጫ ካርድ የመጨረሻ ግቡ የአገልግሎት አቅርቦትን ጥራት እና ተደራሽነት ማሻሻል ነው።

## የተጋላጭና ትኩረትየሚሹ ዜጎች ገፅታ

ከኢሳፕ2 ቁልፍ ገፅታዎች አንዱ ለተጋላጭና ትኩረት ለሚሹ ወገኖች የሚሰጠው ከፍተኛ ትኩረትና በአገሪቱ ዘጠኙም ክልሎችና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ወጣቶች እና ሴቶች ሙሉ በሙሉ በመርኃግብሩ መታቀፋቸውን ማረጋገጥ ነው። የሥራ አመራር ኤጀንሲው ፈጻሚ አጋሮቻችን የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት በሚተገብሩባቸው ወረዳዎች የተጋላጭ ሰዎችና ትኩረት የሚሹ ተሳትፎን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተጥሎበታል።

ደረጀ አባይነህ የ39 ዓመት ጎልማሳ ሲኾን፣ ከደቡብ ክልል ወረዳዎች በአንዱ ውስጥ ይኖራል። በቅርቡ ኢሳፕ2 ከሚተገበርባቸው 142 ወረዳዎች በአንዱ መርኃግብሩ በይፋ በሚጀመርበት አውደ ጥናት ላይ በአጋጣሚ ነበር ያገኘነው። በመርኃግብሩ ደስተኛ እንደሆነ፣ ነገር ግን ስለ ማኅበራዊ ተጠያቂነት የበለጠ ለማወቅ እንደሚፈልግ ነግሮናል። ደረጀ ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደሙ የሚገኝ ሲኾን፣ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት እየወሰደ ይገኛል። የሚወስዳቸው መድኃኒቶች በህይወት የሚያቆዩት ከመሆናቸው ባሻገር ሠርቶ ለመኖርም አስችለውታል። የ3 ዓመት ህፃን ልጅ አባት እንደመሆኑ፣ ቤተሰብ የማስተዳደር ኃላፊነቱን ለመቀጠል ችሏል። አንዳንድ ጊዜ በአካባቢው በሚገኘው ክሊኒክ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒቱ ክምችት መሟጠጥ ያሳስበዋል። የኤች.አይ.ቪ. ህክምና የተቋረጠ እንደሆነ፣ በደም ውስጥ ያለው ቫይረስ መድኃኒቱን ይላመደውና ታማሚው ወደሞት ሊያመራ ይችላል። ደረጀ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒቶች ራሱ እና ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ማኅበር በቀጣይነት የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲረጋገጥ በቁርጠኝነት ተነስቷል።





## ኢሳፕ2 በበይነመረብ

የማኅበራዊ ተጠያቂነት ድምፆች በበይነመረብ ዓለም (digital world) አማካይነት ይበልጥ ትኩረትና ተሰሚነት እንዲያገኙ በመሻት፣ እነሆ ለኢሳፕ2 በፌስቡክ፣ በትዊተር፣ በሊንክድኢን እና በዩቲዩብ ማኅበራዊ ሚዲያዎች አካውንቶች ተከፍተዋል።

የፌስቡክ ገፃችን በመረጃ ሰጪ ይዘቶች በየጊዜው የሚዳብር ሲሆን፣ ይህም በሥራ አመራር ኤጀንሲው፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አባላትና በሌሎች ባለድርሻዎች መካከል እያደገ የሚሄድ መስተጋብር በመፍጠር በማኅበራዊ ተጠያቂነት ውይይቶች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያበረታታል።

የመፈክር ውድድርን የመሰሉ እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ፣ ወዳጆችና ደጋፊዎች የጋራ ሐሳብን ለማራመድ የግል ሐሳባቸውንና ምክረሐሳባቸውን እንዲያካፍሉ በመጋበዝ የመልዕክት ግንኙነቶችን ያለማቋረጥ እያመቻቸን እንገኛለን።

በቀጣዮቹ ወራት የኢሳፕ2ን ገፅታ ከዚህም በላቀ ሁኔታ ለመገንባት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የራሳቸውን ገፅታ እንዲፈጥሩ ለመርዳት እንዲሁም በማኅበራዊ ሚዲያ አውታሮች መካከል ያለውን የእርስበርስ መናበብ ለማጠናከር እያቀድን እንገኛለን።

የኢሳፕ2 በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ መገኘት ዋነኛ ራዕይ በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ተጠያቂነት ጉዳይ ማዕከል መሆን ነው።

ከእኛ ጋር የመልዕክት ልውውጥ ያደርጉ ዘንድ ወደ @esap2 እንጋብዝዎታለን።

ይህ በአለም ባንክ የሚተዳደረው በለጋሾች የአደራ ፈንድ የሚረዳው የኢሳፕ2 (ESAP2) የዜና መጽሔት ነው።

Irish Aid
Government of Ireland
UKaid

MANAGEMENT AGENCY
GOPA WORLDWIDE CONSULTANTS
VNG International
YCI የም አማካሪ ተቋም YEM – CONSULTANT INSTITUTE

Cape Verde st. | P. O. Box 28024/1000
WMA Sets Bldg, 2nd Floor | Addis Ababa, Ethiopia
info@esap2.org.et | Facebook: ESAP2

Reha Touch: 091-120 9525

Ethiopia Social Accountability Program Phase 2